ስለ ቀስተ ዳመና ሬድዮ ማስታወሻ

Aug - 1997

**ክፍል አንድ** አጠቃላይ መግቢያ

ራድዮው የሚቋቋመው በፖሪሱና በአዲስ አበባው የሰላምና እርቅ ጉባኤያች መንፈስ በሃገራችን ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ ለሚገነባ የኢትዮጵያ አንድነት የሚደረገውን ትግል ለማገዝ ነው:: ይህ ዓላማ ዝርዝር ባለ መልኩ ሲቀርብ ሶስት ዋና ዋና ይዘቶች ይኖሩታል::

1ኛ/ በሃገራችን ታሪካዊና የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ለሰላም መታገል ማለት ስለሰላም መልካምነትና ስለጦርነት ክፋት ከመስበክ አልፎ መሄድን ይጠይቃል::ሰላም ማለት የሰው ልጅ መብት መከበር፣ የዲሞክራታይዜሽኑ ሂደት ሥር መስደድ፣በሃገሪቱ ብሄሮች መሃከል የወንድማማችነት መንፈስ መስፈን፣የማህበራዊ ፍትህ ዓላማ ማንሰራራት ማለት ነው:: በመሆኑም ራድዮው እነዚህን ዓላማያች የሚያደናቅፉ ኃይሎችን ይታገላል፣ እነዚህን ዓላማያች ለማራመድ የሚሹ ኃይሎችን ይደግፋል ማለት ነው::

2ኛ/ የወሰደውን ጊዜ ቢወስድም የሃገራችን ችግር የሚፈታውና ዘላቂ ሰላም በኢትዮጵያ የሚሰፍነው በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አማካኝነት በፕሮፖርሽናል ሪፕሬዜንቴሽን/ተመጣጣኝ ውክልና/ የምርጫ ስርዓት መሠረት የህገ መንግሥት ጉባኤ ተሰይሞ የህብረተሰቡን ድጋፍና አክብሮት የሚያገኝ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግሥት ሲኖር ነው:: በመሆኑም ራድዮው ወደዚህ የሚደረገውን ጉዞ በተቻለው ለማገዝ ይጥራል::

ከፍ ብለው የተጠቀሱት ነጥቦች በመጀመሪያ የፖሪሱ ጉባኤ ተሳታፊ ሰባት ድርጅቶች ጸድቆ ለአዲስ አበባው ጉባኤ በቀረበው የመንደርደሪያ ሰነድና ከዚያም የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ባጸደቀው ለአዲስ ዲሞክራሲያዊ ጅማሮ በሚለው ሰነድ ውስጥ ተዘርዝረው የተቀመጡ ስለሆነ እነዚህን ሰነዶች ለሥራችን እንደ ቋሚ መመሪያ አርገን እንወስዳቸዋለን::

3ኛ/ እነዚህ ዓላማያች ከግባቸው ሊደርሱ የሚችሉት በሬድዮ ስለተብራሩ ብቻ ሳይሆን በሃገሪቱ ውስጥ ለነዚህ የሚታገል ሰፊና ዲሞክራሲያዊ መሠረት ያለው ንቅናቄ እየታገለ ሲያታግልባቸው ስለሆነ የህዝብ አመኔታ ያለው ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ለመመሥረት የሚደረገውን ጥረት በተቻለ መጠን ለማገዝ ጥረት ይደረጋል::

**ክፍል ሁለት** የፕሮግራሞች ይዘትና ዝግጅት

በሬድዮው የሚቀርቡት አራት ዓይነት ዝግጅቶች ናቸው:: እነሱም 1ኛ/ በየፕሮግራሙ የሚቀርቡ ዝግጅቶች 2ኛ/ በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርቡ ዝግጅቶች 3ኛ/ ወርሃዊ ዝግጅቶች 4ኛ/ ልዩ ዝግጅቶች

1ኛ/ በየፕሮግራሙ የሚቀርቡ ዝግጅቶች

ሀ/ ዜና[illegible] ትችት

የሚቀርቡት ዜናዎች ከ10 እስከ 12 ደቂቃ የሚፈጁ ሲሆን በሶስት ዓይነት ሊከፈሉ ይችላሉ:: እነሱም አንደኛ ሁሉም የሰማቸውና ምናልባትም በመንግሥት በራሱ ሚድያዎች የቀረቡ ዜናዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ራድዮው በዚህ ዜና ላይ ለመመለስ ካሰበ ወይ ተጨማሪና መንግሥት የሸሸጋቸውን ጉዳዮች ለማውሳት፣ ወይ የተጣመሙ ሃቆችን አቃንቶ የመንግሥትን ሃሰትና አቀራረብ ለማጋለጥ፣ ወይ ደግሞ በኢህአደግ አጠቃላይ ጸረ ህዝብ ስትራቴጂ ያላቸውን ቦታ ለመጠቆም ይሆናል:: ሁለተኛ የዜና ዓይነት በከፊል የተሰሙ /ለምሳሌ ጅማ የሆነ ነገር ጉንደር ያልተሰማ፣ አዲስ አበባ ስለተከሰተ ድፍን አገር ያውቀዋል ተብሎ የማይታለፍ፣ በውጭ ሚድያዎች በሌላ ቋንቋ የቀረበ ወዘተ/ ዜናዎችን ይመለከታል:: በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ስለሚካሄዱ ትግሎች፣ ስ

ለሚፈጸሙ የህዝብ መብት ረገጣዎች ወዘተ ዜናዎች ይቀርባሉ:: በስተኛው ጩርስ የማይታወቁ ወይም የተሸሸጉ ዜናዎችን ይመለከታል:: እነዚህ ሲቀርቡ በቅድሚያ በሃቀኛነታቸው የተረጋገጡ ካልሆኑ ከጊዜ ብዛት የህዝብን አመኔታ ሊያሳጡን ስለሚችሉ ከመቀረባቸው በፊት በውል መረጋገጥ አለባቸው::

ለ/ ትችት

ይህ ከሶስት እስከ አምስት ደቂቃ የሚወስድ ሲሆን በእለቱ ከቀረቡት ዜናዎች በአንዱ ላይ ተመልሰን አስተያየት የምንሰጥበት ዝግጅት ነው::

ሐ/ የጋዜጦች ትችት

ከ5 እስከ 7 ደቂቃ የሚፈጅ ዝግጅት ነው:: አቀራረቡ ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ በወቅቱ ገኖ በታየ በአንድ ክስተት ላይ የተለያዩ ጋዜጦች የሰጡት አስተያየት ሲሆን ሌላ ጊዜ ደግሞ በተለያዩ ክስተቶች ላይ የተለያዩ ጋዜጦች የሰጡት አስተያየት ሊሆን ይችላል:: ትችቱ እንደአስፈላጊነቱ የመንግሥት ሚዲያዎች /በተለይ ራዲዮ/ የሚያስተላልፉትን ቅጥፈትም ሆነ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ አጸፋ ለመስጠትም ሊሆን ይችላል:: ይህ ዝግጅት የውጭ ጋዜጦች ስለኢትዮጵያ ሁኔታ የጻፉትን ዜናና አስተያየት የሚጨምር ሲሆን ይህናው ክፍል በውጭ ተባባሪዎች የሚዘጋጅ ይሆናል::

አላላክና ቅንብርን በተመለከተ በ ሀ ለ ሐ የተጠቀሱት አስቸኳይ ስለሆኑ ከውጭ የሚመጡት በቦኑ አድራሻ በፋክስ ይላካሉ:: ከሃገር ቤት የሚመጡት በፍጥነት ስለሚተላለፉበት ዘዴ በውይይት መስመሩ ይዘረጋል::

2ኛ/ በየአስራ አምስት ቀኑ አንዴ የሚቀርቡ ዝግጅቶች

ሀ/ ስለማህበራዊ/ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች፣ ችግሮችና ትግሎች የሚያትት ዝግጅት /ስሙ ገና አልተገኘም/ እዚህ ላይ ማቀረብ የሚፈለገው ለሰሰፁ ኢኮኖሚክ ህልውናቸው፣ ለጋራ መብታቸው ወይም ጥቅማቸው በቋሚነት ተደራጅተውም ሆነ /ለምሳሌ የተለያዩ የሙያ ማህበራት/ ወይም ደግሞ በአንድ የጋራ ጥያቄ ዙሪያ በግዜያዊነት ተሰባስበው የሚታገሉ ዜጐችና የህብረተሰብ ክፍሎች ስለችግራቸውና ስለትግላቸው የምናትትበት ዝግጅት ነው:: ይህ ዝግጅት ለምሳሌ በሥራ አጦች፣ ከሥራ በተባረሩ ዜጐች፣ በወዛደሮች፣ በነጋዴዎች፣ በገበሬዎች በወጣቶች ወዘተ ችግርና ትግል ዙሪያ ሊሆን ይችላል:: ዝግጅቱ በረፖርታዥ መልክ ከባለጉዳዮቹ ከራሳቸውም ሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ምሁራን በተሰጡ አስተያየቶች የታጀበ መሆን ይኖርበታል:: በተለየ አጋጣሚ ለእንደዚህ ዓይነቱ ፕሮግራም የሚሆን ክስተት በውጭ አገር ካልታየ በስተቀር ፕሮግራሙ የሚዘጋጀው አገር ቤት ባሉ ተባባሪዎቻችን ነው:: ስለአላላኩ ዘዴ በውይይት ይወሰናል::

ለ/ የአድማጮች መልእክት::

ይህ ዝግጅት ከአንድ ወር በኋላ ይጀምራል:: እስከዚያ በተደጋጋሚ ለአድማጮች መልእክት፣ አስተያየትና ጥያቄ እንዲልኩ የፋክስና የፖስታ አድራሻ ይሰጣል:: ለአስተያየቶቹ አስተያየት፣ ለጥያቄዎቹ መልስ የሚሰጥ አንድ ተባባሪ ተመድቧል::

ሐ/ ሲቪክ ትምህርት

ስለሰው ልጅ መብቶች፣ ነጻ ምርጫ፣ ህገ መንግሥት፣ የህግ የበላይነት፣ ወዘተ ትምህርታዊ ዝግጅቶችን ይይዛል:: ኢሰመጉ ከፈለገ በዚህ ዝግጅት እንዲሳተፍ ደብዳቤ ተጽፏል:: ካልተስማማ እዚሁ እውጭ ይዘጋጃል::

መ/ ወንድማማች ህዝብ

ይህ ዝግጅት በአጭር ጊዜ ሲታይ የኢህአዴግን የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካና በህዝቦች መካከል ሊነዛ የሚሞክረውን የጥላቻ መርዝ ለመቋቋም በረዥም ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሄሮች አንድነታቸውን በህግ በተደነገጉ መብቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በጋራ ታሪክና በጋራ ዴስቲኒ ስሜት እንዲገነቡ የሚቀሰቅስ አምድ ነው:: የተለያዩ አክራሪዎች የሚክዱትን የጋራ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ህያውነት፣ ከሚነዛው የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ባሻገር በየብሄሩ ህዝቦች መካከል ያለውን የወንድማማችነት መንፈስ ጥንካሬ በተለያዩ ፕሮግራሞች ለማሳየትና ለማጉለበት እንሞክራለን:: ይህንን ዝግጅት በተመለከተ ጉዳዩን በሃላፊነት የሚይዘው ተባባሪ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ላሉ ተባባሪዎች የፕሮግራም ሃሳብ በቅድሚያ እያቀረበ ዝግጅቱ ስኬታማ እንዲሆን ያደርጋል::

3ና/ ወርሃዊ ዝግጅቶች

እነዚህ ዝግጅቶች በወር አንድ ጊዜ ለአድማጮች የሚቀርቡ ሲሆኑ የሚፈጁት ጊዜ ከአስር እስከ አስራ ሁለት ደቂቃ ይሆናል:: ለእያንዳንዳቸው አንድ ተባባሪ በባለቤትነት የሚመደብ ሲሆን ይህ ተባባሪ ለዝግጅቱ የሚያስፈልገውን ርዳታ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉ ተባባሪዎች ሊጠይቅ ይችላል:: የዝግጅቶቹ ዝርዝር፣

ሀ/ የሰላም ትግል ስለሰላማዊ የትግል ስልት ምንነት፣ እንዲያብብና እንዲሳካ መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ወዘተ የሚቀሰቅስ ዝግጅት ሲሆን ምናልባት ስሙን የሰላም ግንባታ ማለት ያስፈልግ ይሆናል:: የሚሰናዳው ውጭ ነው::

ለ/ ነጻ ዓምድ ግለሰቦች በጽሁፍም ሆነ በኢንተርቪው መልክ ሃሳባቸውን የሚገልጹበት፣ ባለሙያዎችና ምሁራን በሚመለከታቸው መስክ የሃገሪቱን ችግሮች ከነመፍትሄ ሃሳቦችና አማራጮች የሚተነትኑበት ዓምድ ነው:: የተመደበው ሃላፊ ከውጭ ሲሆን ሊያሰናዳ በሚሞክረው ፕሮግራም ሌሎች ሃሳብ ሊሰጡ፣ የሚሳተፉ ዜጎች ሊጠቁሙ ይችላሉ:: ጥያቄውም ሆነ ጥቆማው የሚደረገው በቦኑ ማእከላዊ አድራሻ አማካኝነት ነው::

ጠ/ ዓለም እንዴት ሰነበተች በወሩ ውስጥ በዓለም የተካሄዱትን ዋና ዋና ክስተቶች እየጠቆሙና እየተነተኑ የሚያቀርቡ ዝግጅቶች ናቸው:: የዝግጅቱ ሃላፊ ውጭ ካሉ ተባባሪዎች ውስጥ ነው::

መ/ ወሬ በአካባቢያችን ስሙ እንደሚያመለክተው በአፍሪካ ቀንድ ሃገሮች ስላለው ውጥንቅጡ የወጣ ፖለቲካ፣ ይተነተንበታል:: ዝግጅቱ ውጭ ይሠራል::

ሠ/ ሪፖርታዥ በወሩ ገኖ በታየ ጥያቄ ወይም ትግል ዙሪያ ወይም ደግሞ ጉልቶ ባይታይም መሠረታዊ ጥያቄ ተብሎ ሊታይ በሚችል ጉዳይ /ለምሳሌ ነጋዴዎችና የቤት ኪራይ ጭማሪ፣ የመሬት ጥያቄና የገበሬዎች መፈናቀል፣ የትምህርት ቋንቋ ውዝግብ በደቡብ ከተሞች፣ ወዘተ/ የባለጉዳዮችንም ሆነ የባለሙያ ምሁራንን አስተያየት ያካተተ ዝግጅት ነው:: የሚሠራውም አገር ቤት ባሉ ተባባሪዎች ነው::

ረ/ የሌሎች የትግል ልምድ በአለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአፍሪካ በመካሄድ ላይ ያለው የዴሞክራታይዜሽን ሂደት በአብዛኛው በታ ከሞላ ጎደል የመሳካት ምልክት አሳይቷል /ማለትም ከአፍሪካ ቀንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች በስተቀር/ ከደቡብ አፍሪካ እስከቤኒን፣ ከማዳጋስካር እስከማሊ ከዚያም አልፈን በሌሎች አካባቢዎች ስለተካሄዱ ትግሎች ትምህርት በሚሰጥ መልክ የምናተትበት ዝግጅት ነው:: ምናልባት በዚህ ዝግጅት የወደቁ ለውጦች ብለን የምንጠራቸውን ሂደቶች /ኩንጉ ዛይር ከሞቡቱ በኋላ፣/ ልንተነትን እንችላለን:: የሚዘጋጀው ውጭ ነው::

ሰ/ ሌሎች እንደሚያዩን የውጭ ጋዜጠኞችም ሆኑ ምሁራን፣ የታሪክ ሰዎችም ሆኑ የፖለቲካ ሰዎች ስለኢትዮጵያ የተናገሩት፣ የጻፉት አስተያየት የሚተነተንበት ዝግጅት ነው:: ዝግጅቱ ውጭ ይሠራል:: ለዚህ ዝግጅት የሚሆን ጽሁፍ፣ አስተያየት፣ መጽሃፍም ሆነ ሌላ ማቴርያል የሚያገኙና ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚገምቱ ተባባሪዎች በመአከላዊው አድራሻ በኩል ዝግጅቱን ሊደግፉ ይችላሉ::

ሸ/ የስነጽሁፍ ፕሮግራም ግጥሞች የሚነበቡበት፣ የመጽሃፍ ትችት የሚደረገበት ዝግጅት ነው:: በሃላፊነት አንድ ተባባሪ ቢመደብም ግጥሞችን በመላክ፣ የሚተቹ መጽሃፍትን በመጠቆም ወይም በመተቸት ሌሎችም ተባባሪዎች ሊሳተፉ ይችላሉ::

4ና/ ልዩ ዝግጅቶች

እነዚህ ከታሪካችን በተያያዙ ቀናት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከበሩ ልዩ ቀናት ወዘተ አካባቢ ከወዲሁ ፕሮግራም ተይዘላቸው የሚዘጋጁ ናቸው:: አስተባባሪው ውጭ የሚገኝ ተባባሪ ቢሆንም ሃገር ውስጥ ያሉ ተባባሪዎች ዶኩሜንት በመላክ፣ ከባለሙያዎች ኢንተርቪው በመልቀም ወዘተ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል:: ስለእያንዳንዱ ዝግጅት ዝርዝር እቅድ ማውጣትና ትብብር መጠየቅ ውጭ ያለው ሃላፊ ተግባር ይሆናል:: ለጊዜው ሊጠቀሙ የሚችሉ የልዩ ዝግጅት አርእስቶች፣

1/ በኦክቶበር ዓለም አቀፍ ጸረ ርሃብ ቀን 2/ በዲሴምበር ዓለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት ቀን 3/ የካቲት 12 4/ የካቲት 23 ዓድዋ 5/ የካቲት 25 የመሬት አዋጅ የታወጀበት ቀን 6/ ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን 7/ ሜይ ደይ 8/ በጁን ወር ዓለም አቀፍ የነጻ ፕሬስ ቀን 9/ በጁን ዓለም አቀፍ የልጆች መብት ቀን ወዘተ ናቸው:: ዝርዝሩ ወደፊት ይላካል::

## ቀስተ ዳመና ሬድዮ /በውጭ ለሚገኙ ተባባሪያች ማስታወሻ/

ይህ ማስታወሻ የሚደርሳቸው ሁሉ በሚገኙበት አገር ለራድዮው ተባባሪ ሊሆኑ የሚችሉ ተ
ወካዮች ወይ አንድ ግለሰብ ወይ ደግሞ አንድ ኮሚቴ ሰይመው አድራሻውን/አድራሻዋን ስ
ልክና ፋክስ ቁጥር በቶሎ ማስታወቅ ይኖርባቸዋል:: ወዲያውኑ የግንኙነት መስመር ይዘ
ረጋላቸዋል:: ከውጭ ወኪሎቻችን የሚጠበቀው ዋና ተግባር ከቀላ ጉደል እንደሚከተለው
ሊዘረዝር ይቻላል፣

1ኛ/ በየፕሮግራሙ ለሚቀርቡ ዜናዎች ከአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን ዜናዎች ከ
ሥር ከሥሩ ማስተላለፍ:: እነዚህ ዜናዎች ከአካባቢው የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ፣ በሃገሩ ካ
ሚታተሙ ጋዜጦችና መጽሄቶች የተለቀሙ ዜናዎችና ትችቶች፣ በሃገሩ ከሚገኙና ስለኢትዮጵ
ያ ያገባናል የሚሉ ኤን.ጂ.ኦዎች የተገኙ መግለጫዎች ወይም አቋሞች፣ የመንግሥት አካ
ላት ወይም የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች የወሰዷቸው አቋሞች፣ የኢትዮጵያን ሁኔታ የሚከ
ታተሉ የባእድ ምሁራን ካቀረቧቸው ራፖርቶች ወይም ሌላ ጽሁፎች፣ የስብሰባዎች/ውሳኔዎች
ዘገባ... ተለቅመው የሚላኩ ናቸው::

2ኛ/ የጋዜጦች ትችት የሚለው በአመዛኙ የአገር ቤት ጋዜጦችን የሚመለከት ቢ
ሆንም በያለበት የሚገኙ የባእድ ጋዜጦች ስለኢትዮጵያ ያሰፈሩት ዜናና አስተያየቶች በ
ትችት መልክ ይቀርባሉ:: በመሆኑም በተባባሪነት የተመደቡ ሁሉ በአካባቢያቸው የሚወጡ
ጋዜጦችን እየተከታተሉ ዜናና ትችት ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

3ኛ/ ሌሎች እንደሚያዩን ለሚለው አምድ/ዝግጅት/ ማቴርያል የሚጠበቀው በውጭ
ከሚገኙ ተባባሪያች ነው:: ይህ ስለኢትዮጵያ ጊዜያዊም ሆነ ታሪካዊ ሁኔታ፣ በሃገሪቱ
የፖለቲካ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ስለኢኮኖሚዋ፣ ስለህዝቧ ባህል፣ ስለወደፊት እድሏ በስ
ብሰባዎች ላይም ሆነ በሌሎች ጽሁፎች የባእድ ምሁራን፣ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ሰዎች የ
ሰጡትን አስተያየት የሚመለከት ነው:: ተባባሪያች ከቻሉ ራሳቸው ተቸተው ዝግጅታቸውን
ሊልኩ ይችላሉ:: ይህ ካልሆነላቸው ጥሬውን ማቴርያል ወደራድዮው ልከው ሥራው ለዚህ
ዝግጅት በሃላፊነት በተመደበው ተባባሪ ይሰራል::

4ኛ/ ስለአጠቃላዩ ዝግጅት ዝርዝር ሰንጠረዥ አያይዘናል:: ተባባሪያቻችን ለ
ተለያዩ ዝግጅቶች አስተዋጽኦ ማድረግ ከቻሉ ጥሩ ነው::